# የዕምነት ነፃነት ከህገ መንግሥት እስከ ግለሰብ

ይመር 3/14/12

ዓለማችን የተለያዩ ዕምነት ተከታይ ወገኖች አለም ነች፡፡ እዚህም ሆነ እዚያ ለሁላችንም እኩል - የጋራ ነች፡፡ በሀገር ደረጃ ስንመጣም ያለው እውነታ ተመሳሳይ ነው፣ አገር የጋራ ነች፡፡ የኢትዮጵያ ህገመንግስት ተገቢውን ሥፍራ ከሰጣቸው ነፃነቶች አንዱ ይኸው የሃይማኖት ጉዳይና የዜጎች የእምነት ነጻነት ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ማንኛውም ዜጋ የመሰለውን ሃይማኖት መከተል ይችላል፣ ባጠቃላይም የእምነት ነጻነቱ ሙሉ ለሙሉ ተከብሯል፡፡ መንግሥትና ሃይማኖትም የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህን ትልቅ ጉዳይ  ልብ ብሎ ለተመለከተው ለሀገራችንም ሆነ ለኛ ለዜጎች ትልቅ እርምጃ ነው፡፡

የሀገራችንን ህገ መንግሥት የዕምነት ነፃነትን  በተመለከተ ይህን ስንል ሌላ ጥያቄ ተከትሎ የሚመጣ ይመሰለኛል፡፡ ይህም "ህገመንግሥቱ ላይ የሰፈረው የሃይማኖት ፅንሰ ሀሳብና የዕምነት ነፃነት ጉዳይ ምን ያህል እኛ ውስጥ ሰርፆ ተግባራዊ እያደረግነው ነው?" የሚለው፡፡ የጽሁፉ ርእሰ ጉዳይም የሚያጠነጥነው በዚህ ዙሪያ ላይ ነው፡፡

በአለማችን በርካታ ዕምነቶች እንዳሉ ሁሉ የተለያዩ ዕምነት ተከታይ ወገኖችም አሉ፡፡ ሁሉም እንደየሀገሩ ባህል ተከባብሮና ተቻችሎ፣ ልዩነትን ተረድቶና በሁላችንም ዘንድ በልዩነት ውስጥ አንድነትን ፈቅደን ለዘመናት በሰላምና በአብሮነት መንፈስ እየኖርን ነው፡፡ በሰላም ከሚኖሩት፣ በመከባበርና በመቻቻል ባህላቸው በምሳሌነት ከሚጠቀሱት ሀገራት መካከልም በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት ጥቂት ሀገራት መካከልም ሀገራችን ኢትዮጵያ አንዷ  ናት፡፡

ዓለማችን በርካታ ሃይማኖቶችንና የሃይማኖት ተከታዮችን እያስተናገደች ነው ስንል ምንም አይነት የሃይማኖት ግጭቶችን አላስተናገደችም ማለት ግን አይደለም፡፡ በርካታ የታሪክ ድርሳናትን ስንመረምር መነሻቸው ሀይማኖት የሆኑ ግጭቶችን እንመለከታለን፡፡ ኢትዮጵያ በሀይማኖት አለመቻቻል ወይም በዚህ ሳቢያ በተፈጠረ የከፋ የእርስ በርስ ግጭትና እለቂት ስሟ ተነስቶ አያውቅም፡፡ ይህ ሁላችንንም ሊያስደስትና ሊያኮራን ይገባል፡፡ ይህን አኩሪ ታሪክ አጠናክሮ የመቀጠሉ ጉዳይም የኛ፣ በተለይም አሁን ያለነው ኢትዮጵያውያን ሀላፊነት ነው፡፡ ነገር ግን ይህን እውነታ በመርሳትና እንደሌለ በመቁጠር፣ አገሪቷ የዕምነት ነፃነትን የመፍቀድ

ህገመንግስት የሌላት በማስመሰል በሻይ ብርጭቆ ውስጥ ማዕበል ለማስነሳት የሚጥሩ ወገኖች አልፎ አልፎ መታየታቸው አልቀረም።

እዚህ ላይ በተለያዩ አንዳንድ ሀገራት ለሀይማኖት አለመቻቻል መነሻ ሰበቡ ምንድነው? የሚለውን አቢይ ጥያቄ ማንሳትና ጥቂት ነጥቦችን በመጠቃቀስ የተወሰኑ ሀሳቦችን ማንሳት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በተለያዩ ተመራማሪዎች ዘንድ ተቀባይነትን ያገኙት የአለመቻቻል ወይም የግጭት መነሻዎች በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ "እኔና የኔ ብቻ ነው ልክ/ዕውነት፣ የሌላው ሁሉ የተሳሳተ ነው፤" የሚል አመለካከት በጥቂቶች ዘንድ መኖርና የራስን ከፍ የሌላውን ግን ዝቅ አድርጎ ማየት´ እንደሆኑ ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ከሚገለፅባቸው መንገዶች አንዱ "ፍረጃ" (Labeling) ሲሆን ሌሎች በርካታ ከነዚህ ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ምክንያቶችም  አሉ፡፡ ለጊዜው ከፍረጃ ጋር የተያያዙ  ችግሮችን እንመልከት። ፍረጃ ብዙ ጊዜ የሚታይና የሚሰማ፣ እጅግ በጣም አሳሳቢ የሆነና የሃይማኖትን ጨምሮ ለሌሎች በርካታ   ግጭቶች መነሻ ሊሆን እንደሚችል በዚህ ዙሪያ የተካሄዱ አንዳንድ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

ዛሬ አለማችን በየዕለቱ በርካታ አደጋዎችንና ወንጀሎችን ታስተናግዳለች፡፡ እነዚህ ወንጀሎች ተወደደም ተጠላም በሰዎች በግል ወይ በቡድን ደረጃ የሚከናወኑ ናቸው፣ ነገር ግን ችግሩን ከግለሰብ ወይም ከቡድኑ የግል ባህርይ፣ ፍላጎትና አላማ አንፃር መርምሮ  ውሳኔ ላይ ከመድረስ ይልቅ ከቡድኑ/ ግለሰቡ ኃይማኖት አንፃር ብቻ በማየት የቡድኑን /ግለሰቡን ተግባር እሱ ወይም ቡድኑ የሚከተለውን ሃይማኖት/ እምነት ተከታዮች ሁሉ ወንጀሉን እንደፈፀሙት አድርጎ በመቁጠር ሃይማኖቱን /የዕምነት ተቋሙን ተጠያቂ የማድረግ ነገር በአለማችን የተለያዩ ክፍሎች ሲስተዋል ቆይቷል። ይህም፣ እንደብዙዎች አተያይ፣ ችግሩን ከማባባስና ለግጭት ሰፊ በር ከመክፈት ያለፈ የፈየደው አንዳችም ነገር የለም። በመሆኑም ወንጀለኞች ጥፋተኞችን ከራሳቸው ከግል ማንነታቸው አንፃር ማየት እንጂ ከሃይማኖታቸው ወይም ከሚከተሉት ዕምነት አንፃር በመፈረጅ የተሳሳተ ማጠቃለያ ላይ መድረስ ተገቢ አይደለም። ለተፈጠረው ችግርም ምንም አይነት የመጨረሻ መፍትሄን አያስገኝም።

ሳራ /Sara Ziejle/ የተባሉ ፀሐፊ (America Now, 1999 ላይ እንደሰፈረው) ለአለመቻቻል መነሻዎቹ በርካታ ሲሆኑ አንዱ በሀገራት ህገመንግስታት ላይ የሰፈረውን የዜጎችን የመናገር ነፃነት (Freedom of expression)ን በአግባቡ አለመረዳትና በተሳሳተ መንገድ የሌሎችን መብት በሚዳፈር መልኩ መጠቀም ነው። ይህ ደግሞ አንዱ የሌላውን አጠቃላይ ማንነት

አለማክበርን (Lack of respect) ያስከትላል። ለዚህ ደግሞ ቁልፉ መፍትሄ መከባበር (respect) ነው።

ማልቪን ሮድስ የተባሉ ተመራማሪን ጨምሮን በርካታ ፀሐፍትና ተመራማሪዎች በዘመናችን ያለው የሃይማኖት አለመቻቻል መነሻውም ሆነ የችግሩ ባለቤት ይኸው የዘመኑ ሰው፣ በተለይም ሁለተኛውና ሶስተኛው ትውልድ፣ እንጂ ቀደም ሲል በአለማችን፣ በአያት ቅድመ አያቶቻችን ዘንድ የነበረ ክስተት አለመሆኑን "Surprisingly, most of the [religious] intolerance seems to come from the second and third generations,  who are more radical" በማለት ይገልፁታል። ህገመንግስቱ ለዜጎች የሰጠውን መብት በተፃረረ መልኩ አንዱ የሌላውን የእምነት ነፃነት አለማክበር (disrespectful act)፣ በሃይል የራስን እምነት ለማስፋፋት ከመፈለግ የሚመነጭ አደገኛ የግለኝነት አባዜ ነው፡፡ የሌላውን የእምነት ነፃነት፣ ሃሳብን በነጻነት የመግለፅ፣ የመሰብሰብና የመደራጀት መብቶች ወዘተ የመሳሰሉትን በተቃራኒው በመተርጎም ለጥፋት ተግባር ማዋል የሌሎችን መብት መግፈፍ ነው፡፡  በእስካሁኑ የሰው ልጆች የአብሮነት ትስስር  ወስጥ በመከባበር ላይ የተመሰረተውን ህብረ-ባህላዊነት (multi-culturalism) እና ሌሎች ልዩነቶችን ባለመገንዘብ አለያም ሆን ብሎ በመደፍጠጥ የማህበረሰቡን መልካም ኑሮ ለማናጋት መሞከርና ለዚህ ተግባርም ሃይማኖትን በሽፋንነት በመጠቀም የስልጣን ማግኛ ወይም የግል ፍላጎትን ማሳኪያ አቋራጭ መንገድ ማድረግ እጅግ አደገኛ አካሄድ ነው፡፡ በአለም ላይ እየተስተዋለ ላለ የአለመቻቻል (intolerance) በመንስኤነት የሚጠቀሱ በርካታ ሰንካላ ምክንያቶችም በየጊዜው እየተፈበረኩ ለግጭትና አለመግባባት መንስኤ እየሆኑና ችግሮችን ይበልጥ እያወሳሰቡ ይገኛሉ፡፡ በዚህ አይነት የጥፋት መንገድ ላይ እየተጓዙ ያሉ የጥፋት ሃይሎችን  አለም እያወገዛቸው ያለውም በዋነኛነት ለዚህ ነው። ለዚህም ነው ንጹሃን በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ተታልለው የእነዚህ በሃይማኖት ሽፋን የግል ጥቅምን ለሚያሳድዱ ጥቂት ፅንፈኛ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች አባሪ ተባባሪ ወይም ሰለባ እንዳይሆኑ የእምነትና የሲቪክ ተቋማት እንዲሁም ሰላም ወዳድ ኃይሎች ሁሉ በአንድ ድምፅ ስለ ሰላምና መቻቻል እያስተማሩ ያሉት።

ሀገራችን በሀይማኖት መቻቻል በኩል አኩሪ እሴትና ባህል የማዳበራችንን ያህል  አሁን አሁን አልፎ አልፎም ቢሆን ችግር ለመፍጠርና አብሮነታችንን ለመቦርቦር የሚንቀሳቀሱ ጥቂት ግለሰቦች ወይም ኃይሎች የሉም ማለት ግን አይቻልም። ኢትዮጵያዊ ሆነው የኢትዮጵያን ህዝብ ማንነት በውል የማያውቁ፤ቢያውቁም ህዝቡ በቀላሉ እየተነሳ የሚጋጭ እየመሰላቸው የሚችሉትን ሁሉ ለማድረግ የተማማሉና አልፎ አልፎም ይህንኑ እኩይ ተግባራቸውን ለመተግበር የሞከሩ ጥቂት ኃይሎች አልጠፉም። ከነዚህም ውስጥ አንዱ በጥበብ ስም በተለያዩ

"ኪነ-ጥበበኞች" በየጊዜው በሲዲ ቅጂ የሚለቀቁ በዘለፋ የተሞሉ ግጭት ቀስቃሽ የእምነት ስብከቶችና ዝማሬዎች እንደነበሩ ብዙዎቻችን ታዝበናል፡፡ ይህ ደግሞ ህገመንግስቱ ለዜጎች ያጎናፀፈውን የዕምነት ነፃነት የሚቃረን በመሆኑ በእጅጉ የሚወገዝ ተግባር ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ቢሳካላቸውና የተመኙት ግጭት ቢከሰት የሚያገኙት ጥቅም ምን ይሆን? ትክክለኛው የሃይማኖት አስተምህሮ በርግጥስ ይህን የነሱን እኩይ ድርጊት ይፈቅዳልን? ለጊዜው እነሱ የሚሰጡንን መልስ ባናውቅም በኛ በኩል ግን መልሳችን "በጭራሽ" የሚል ነው።

እነዚህ ወገኖች አንድ ያላገናዘቡት ነገር ቢኖር አገሪቱ ኢትዮጵያ ህዝቡም ኢትዮጵያዊ መሆኑን ነው። ለዘመናት ተቻችሎና ተግባብቶ የኖረን ህዝብ ባልበሰለና ምንም ዓይነት ተጨባጭና አሳማኝ አመንክዮ በሌለው ሰንካላ ዲስኩር አጋጨዋለሁ ብሎ መነሳት አንድ ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ላይ መውደቅ ነው። የኢትዮጵያን ህዝብ ማንነት ጭራሽ አለማወቅ ነው የሚሆነው። ሰሞኑን አንድ የሃይማኖት አባት በቴሌቪዥን እንደገለፁት ይህ አሁን አሁን በሀገራችን እየተስተዋለ ያለው የተዛባ አስተሳሰብ ኢትዮጵያዊ ባህልና ምንም ዓይነት የታሪክ አሻራ የሌለው፣ በአንዳንድ ጸረ ሰላምና ጸረ ልማት ኃይሎች የሚዘወር መስመሩን የሳተ አካሄድ ነው።

ሰሞኑን በክልሎች አንድ አቢይ ተግባር ሲካሄድ በመገናኛ ብዙሀን ተመልክተናል። የጋራ የሃይማኖት ምክር ቤት ማቋቋም። ይህ ጥሩ ጅምር ይመስለኛል። ነገሩ "ሳይቃጠል በቅጠል" ነውና የጥፋት ሃይሎችን ለማስተማር አንዱና ቁልፉ መንገድ የእነዚህ ምክር ቤቶች መኖር በመሆኑ ሁሉም ክልሎች ምክር ቤቱን በማቋቋም በኩል ተመሳሳይ አቋም ላይ ቢደርሱ መልካም ነው። የሁሉም ሃይማኖት ተከታይ ምዕመናን የጋራ ድምፅ ይኖራቸውና አጥፊዎችን ያስተምሩ ዘንድ የእነዚህ ዓይነቶቹ ተቋማት መኖር ወሳኝ ነው።

ቀደም ሲል በአለም ህብረተሰብ ዘንድ አክራሪነት እየተወገዘ መሆኑን ጠቅሰናል። ለመሆኑ የሃይማኖት አለመቻቻል ወይም ግጭት ለምን ይወገዛል? ውግዘቱ ዝም ብሎ የተከሰተ ወይም ለወጉ ያህል እየተደረገ ያለ ነው? ብለን ብንጠይቅ የምንረዳው አቢይ ቁም ነገር ቢኖር ውግዘቱ ዝም ብሎ ሳይሆን የራሱ የሆኑ ታሪካዊ መነሻዎች ያሉት መሆኑን ነው። በቅርቡ ለንባብ የበቃውን |The Good News´ (Jan. - Feb., 2012) ስንመለከት በአለማችን ላይ በሃይማኖት ሽፋን በተደረጉ ግጭቶች ምክንያት በርካታ ዜጎች ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ ከግምት በላይ የሆነ የንፁሃን ደም ፈሷል፣ ብዙዎች ለስደት፣ ረሃብና እርዛት ተዳርገዋል፣ አሻራቸው እስካሁን ያልጠፉ በርካታ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ተከስተዋል፡፡ ሌሎችም ብዙ ብዙ ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት ተስተውሏል፡፡ ከዚህ አንፃር እዚህ እኛ ጋ፣ አንድን ት/ቤት ተገን አድርጎ እየተደረገ ያለውና የአንድ ሃይማኖት ተከታዮችን ለመከፋፈል እየታየ ያለው ሽኩቻ

ምክንያቱ ምንድ ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለኛል። መንግስትም ምንም እንኳን ቀደም ሲል እንደጠቀስነው በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ የማይገባ ቢሆንም ካለበት የህዝብንና የሃገርን ሰላምና የዜጎችን የዕምነት ነፃነት ከማስከበር መንግሥታዊ ሃላፊነቱ አንፃር አዋኪዎችን ኃይ ሊላቸው ይገባል። የመጅሊስ አመራሮች በሰጡት መግለጫ ላይ የተከሰተውን ችግር ለመፍታት መንግሥት ተገቢውን ጥረት እንዲያደርግ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡ ይህን ተከትሎም ሰላም ወዳድ የዕምነቱ ተከታዮች፣የተለያዩ ኃይማኖቶች አባቶችና ምሁራን ሌላውም የህብረተሰብ ክፍል ሰላማዊና ሕጋዊ ጥረቱን በመደገፍ ከመንግሥት ጎን እንደሚቆሙ አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህ አኳያም መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ሊያደርግና  የድርሻውን ሊወጣ የግድ ነው።

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሀገር እንደመሆኗ የበርካታ የተለያዩ ሃይማኖቶች እምነት ተከታይ ዜጎችም የጋራ ሀገር ናት፡፡ ይህ ደግሞ ፀጋዋ ብቻ ሳይሆን ኩራቷም ነው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ተምሳሌት ያካደረጓት መለያዎቿ መካከልም የልዩነቶች መቻቻል እሴቶቿ ነጸብራቅ የሆነው ይኸው ህብሯ ነው፡፡ አሁን ያለው የሀገሪቱ መንግሥትም ይህንኑ ተገንዝቦ እስከዛሬ በታሪካችን ታይቶ ባልታወቀ ደረጃ የዜጎችን የዕምነት ነፃነት በህገ መንግስቱ ውስጥ በግልጽ የተደነገገው በሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡ መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውንና መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ አፅንኦት ሰጥቶ አስፍሯል፡፡ ሌሎች በርካታ መብቶችና ነፃነቶችንም እንዲሁ፡፡ ይህ ደግሞ አሁን ያለው መንግስት ለማንኛውም ሃይማኖት ያልወገነ ነፃ መንግስት (secular government) ስለመሆኑ አይነተኛ ማረጋገጫ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ለአክራሪዎችና ጽንፈኞች የተመቻቸ ሁኔታ ይኖራል ማለት አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም፡፡ ጥገኛ ኃይሎች ሃይማኖትን ካባ አድርገው አለያም ሌላ ሁኔታ እየፈጠሩ ሃገሪቱንና የዜጎችን ሰላማዊ ሕይዎትና የዕለት ተዕለት ኑሮ ላተራምስ ቢሉ ፈጽሞ ሊፈቀድላቸው አይገባም፡፡  መንግሥት የዜጎችን ነጻነትና መብት ከማስከበር አኳያ ይህን ማድረጉ ደግሞ የሌላው ወገን ደጋፊ፣ የሌለው ደግሞ ተቃዋሚ የሚያስብለው አይሆንም፡፡

ለዚህም ነው ሰሞኑን  "መንግሥት መጅሊስን ይደግፋል" የሚለው አደናጋሪ ሀሳብ ውሃ የሚቋጥር ሆኖ የማይገኘው፡፡ ከሆነስ ጉዳዩ መታየትና መበረታት የነበረበት መንግስት የሙስሊሙን ህብረተሰብ ወንድማማችነት ከማጠናከር አንፃር እያደረገ ያለው ተግባር ከመሆኑ አንፃር ነበር፡፡ ስለእውነት ለመናገር የሙስሊም ዕምነት ተከታዩች ከሌሎች ሃይማኖቶች እኩል የሃይማኖት ነጻነታቸውን አስከብረው እየኖሩ እንደሆነ ሰሞኑን በተደረጉ ውይይቶች ላይ ራሳቸው የዕምነቱ አባቶችና ተከታዮች በአንድ ቃል ያረጋገጡት ሃቅ ነው፡፡

በመሆኑም ሁሉም ወገን በተለይም ሙስሊሙ የህብረተሰብ ክፍል ለጋራ ጥቅም መረጋገጥ ከሌሎች ጋር ተባብሮ መስራትና  አገሪቱ እያካሄደች ያለውን ፈጣን የልማት ግስጋሴ ማገዝ እንዳለበት በውል ተገንዝቦ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ ደግሞ በህገመንግሥቱ ላይ የሰፈሩት የዕምነት ነፃነት መሰረታዊ ነጥቦች በሁላችንም ውስጥ በአግባቡ ሊሰርፁ ይገባል፤ ያኔ ሁሉም ነገር ልክ ይሆናልና፡፡